የሂሳብ ክፍል
ሲዮባን ሙሊጋን፡ የሂሳብ ትምህርት ዲን
617-349-6650 • smulligan@cpsd.us

ጁሊ ዋርድ፡ የ K-12 የሂሳብ ትምህርት አስተባባሪ
617-349-6683 • jward@cpsd.us

መጋቢት 1፡ 2021 ዓ.ም

የተከበራችሁ የ 8ኛ ክፍል ተማሪ ቤተሰቦች/ተንከባካቢዎች፡

በዚህ ያልተጠበቀ እና ለሁሉም አዲስ የሆነ ሁኔታ፡ እስርዎና ቤተሰብዎ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ እንደቻሉ ተስፋ እናደርጋለን። ሁላችንም እንደምናውቀው፡ በዚህ የትምህርት ዓመት በብዙ መድረኮች ላይ የተከሰቱ ለውጦችን ለማስተካከል በፖሊሲዎች፣ በአሠራር ሂደቶች፣ እና በመገናኛዎች ላይ ለውጥ ወይም የሚያስፈልጋቸው ያልተጠበቁ ችግሮች አጋጥመዋል።

ዓላማችን የዲስትሪክቶች የፍትሃዊ አሰራሮችና ተደራሽነት ቁርጠኝነትን በመጠበቅ ይህ አስቸጋሪ የሆነ ጊዜ በተማሪዎቻችን ላይ ሊያሳድረው የሚችል ተጽዕኖ ለማቃለል ነው።

እርስዎ እና ልጅዎ(ልጆችዎ) የ 8 ኛ ክፍል ዓመት በመጨረስ ወደ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጉዞ በመጠባበቅ ላይ እንደመሆናቸው መጠን፡ በዚህ ጊዜ ከ የካምብሪጅ ሪንጅ እና የላቲን ትምህርት ቤት (Cambridge Rindge and Latin School) (CRLS) የሂሳብ ክፍል ጋር ለማስተዋወቅ እንዲሁም እዚህ ላይ የሚቀርቡ የሂሳብ ትምህርት ፕሮግራሞችን በተመለከተ መረጃ ለመስጠት እንፈልጋለን።

የሂሳብ ትምህርት ክፍል፡ የትምህርት ቤቱን ተልዕኮ እንዲሁም የሂሳብ ክፍልን ራዕይ ለማስከበር እና በትምህርቶች፣ ካሪክለሞች፣ እና ሥርዓተ-ትምህርቶች ዙሪያ ውሳኔዎቻችንን ለማሳወቅ ይጥራል።

<u>የሂሳብ ክፍል ራዕይ፦</u>

> ተመጣጣኝ የሂሳብ ትርጉም እንዲኖራቸው ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ ሚዛናዊ የሂሳብ ማህበረሰቦችን ይፈጥራል፣ ለሁሉም ተማሪዎች ፈታኝ የሆነ ሥርዓተ-ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል፣ እንዲሁም በሂሳብ የትምህርት ክፍል ጊዜ ውስጥ ተማሪዎች ትርጉም ባለው ሁኔታ እንዲሳተፉ ያበረታታል። (ብሔራዊ የሂሳብ መምህራን ምክር ቤት)

በ CRLSL፡ አልጀብራ I ለ 9ኛ ክፍል ተማሪዎቻችን በተለምዶ የመጀመሪያ የሂሳብ ክፍል ሆኖ ይሰጣል። አልጀብራ I፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሁሉም የሂሳብ ትምህርታችን ዋናው መሠረት ሲሆን፡ ተማሪዎቹ በሙሉ ስለ አልጀብራ I ጽንሰ-ሀሳቦች እና ደረጃዎች ሰፋ ያለና አጠቃላይ ግንዛቤ ማግኘታቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። በታሪክ እኳያ ሲታይ፡ አብዛኞዎቹ አዲስ የ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች በ CRLS የአልጀብራ I ትምህርት ይወስዳሉ። አልጀብራ I በሙሉ የኮሌጅ መሰናዶ ዓመት (College Preparatory) እና በሙሉ የሴሚስተሩ ጊዜ በላቀ የትምህርት ደረጃዎች (Honors) ይሰጣል።

ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ የሂሳብ ትምህርትን (በተለይም አልጀብራ 1) በ 8ኛ ክፍል የሂሳብ አስተማሪያቸው ለእያንዳንዱ ተማሪ የመማር ችሎታን ብቃት ደረጃ ላይ በመመርኮዝ እንዲወስዱ ምክር ይሰጣቸዋል።

ተማሪዎች ከአልጀብራ I ፕሮግራም ለማውጣት፡ ተማሪዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አልጀብራ 1 ከመደበኛ የኮርስ ትምህርት እንዲያገኙ እድል የሚሰጥ አሰራር አዘጋጅተናል። ይህ ሂደት ከስምንተኛ ክፍል የቅድመ-ምዘና ውጤቶች በመነሳት ከዚህ የፀደይ/ክረምት የትምህርት ጊዜ ጀምሮ የሚሰጡትን የመማሪያ ሞጁሎችን ያካትታል። በሚቀጥሉት ሳምንቶች ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል።

ተማሪዎች በ 8ኛ ክፍል ባሳዩት አስፈላጊ የአልጀብራ ጽንሰ-ሃሳቦች ችሎታ ደረጃ ላይ በመመርኮዝ፡ በ CRLS ውስጥ አልጀብራ I የሚወስዱ ተማሪዎች አንድ ዓመት ሙሉ የአልጀብራ I A/B ክፍል ወይም ከፍተኛ ደረጃ አልጀብራ I (Honors Algebra I) ይሰጣቸዋል። የአልጀብራ I መሰረታዊ ደረጃዎችን እና ጽንሰ-ሀሳቦችን አጠናቆ ያወቁ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ጂኦሜትሪ (Honors Geometry) ለመመዝገብ ይመከራሉ።

የሂሳብ ምደባ ሂደትን በተመለከተ ማንኛውም ጥያቄ ካልዎት እባክዎን አሁን ካለው የልጅዎ የ 8ኛ ክፍል የሂሳብ አስተማሪ ወይም የአመራር አማካሪ ጋር ይነጋገሩ። በተጨማሪ፡ እባክዎን በቀጥታ እኛን ለማነጋገር ነጻነት ይሰማዎት።
እናመሰግናለን፡ እንዲሁም ልጅዎ በ CRLS ቆይታቸው የተሳካ የሂሳብ ትምህርት ጊዜ እንዲሆንለት በተስፋ እንጠብቃለን።

ከሰላምታ ጋር፡

*Julie Ward* *Siobahn Mulligan*

ጁሊ ዋርድ
የ K-12 የሂሳብ ትምህርት አስተባባሪ

ሲዮባን ሙሊጋን
የካሪክሎም እና ፕሮግራም ዲን – የሂሳብ ትምህርት

CAMBRIDGE
PUBLIC SCHOOLS


የሂሳብ ክፍል

ሲዮባን ሙሊጋን፡ የሂሳብ ትምህርት ዲን
617-349-6650 • smulligan@cpsd.us

ጁሊ ዋርድ፡ የ K-12 የሂሳብ ትምህርት አስተባባሪ
617-349-6683 • jward@cpsd.us



ካምብሪጅ የህዝብ ትምህርት ቤቶች
jward@cpsd.us
(617) 349-6683

ካምብሪጅ ሪንጅ እና ላቲን ትምህርት ቤት
smulligan@cpsd.us
(617) 349-6650